# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2014/49*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

**የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ከግሉ ዘርፍ በጤናዉ መስክ የተገኙትን ዉጤቶች ማጠናከር የተሰኘ (ሾፐስ) በጤናዉ መስክ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች የሚያገኙት ድጎማና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ትኩረት የሚያገኝበትን የንግድ ትርኢት አዘጋጀ**

*ይህ አገር አቀፍ ዐዉደ ርዕይ አገልግሎት ሰጪዎች÷ ባለሀብቶችና አበዳሪዎች የሚገናኙበትን መድረክ ፈጥሯል፡፡*

***አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፤ ታሕሣሥ 1 2007 ዓ.ም.፡-*** የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ከኢፌድሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ በጤናዉ መስክ ለተሰማሩ የግል ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ከህዳር 30 እስከ ታህሣሥ 1 2007 ዓ.ም. የቆየ ዐዉደ ርዕይ በሂልተን ሆቴል አዘጋጀ፡፡ ከግሉ ዘርፍ በጤናዉ መስክ የተገኙትን ዉጤቶች ማጠናከር የተሰኘ የፕሬዜዳንቱ የአስቸይ ጊዜ የኤድስ ዕርዳታ ዕቅድ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግለት የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ፕሮጀክት ይኸዉ ዐዉደ ርዕይ የተለያዩ ምርቶችና አገልግሎቶች በሚደጎሙበት ሁኔታዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የግል ዘርፍ በጤናዉ መስክ ያበረከተዉ አስተዋፅኦ የታየበትና ቀጣይ አቅጣጫም የተጠቆመበት ነበር፡፡

በዐዉደ ርዕዩ በጤናዉ መስክ ግንባር ቀደም የሆኑና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ያፈሰሱ ለጋሾች፤ የዳያስፖራ ባለሃብቶች የግሉ ዘርፍ የሚደጉሙ ባንኮች ተሳትፈዋል፡፡ ትኩረት የተደረገባቸዉ *ጉዳዮች በኢትዮጵያ ለጤናዉ ዘርፍ የሚደረገዉ ድጎማ የሚያስፈልገዉ መሻሻል፤ የግሉ የጤና ዘርፍ የሚያደርገዉ የገንዘብ ድጋፍ ተደራሽ ስለሚሆንባቸዉ ሁኔታዎችና አዳዲስ የድጎማ መንገዶች ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡*

*የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ተጠባባቂ ዳይሬክተር ጌሪ ሊንደን የመክፈቻ ንግግር ባደሩጉበት ወቅት፡- ‹‹የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በአሜሪካ ህዝብ ስም ከኢፌድሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከፍተኛ የግብዓት ጥረት ባለበት በዚህ ወቅት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል በሚኖረዉ ሽርክናና አዳዲስ መፍትሔዎችን በማፈላልግ የሚያምኑ፤ በኢትዮጵያ ጠንካራና ዘላቂ የሆነ የጤና ስርአትን ለማረጋገጥ ጠንክረዉ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት የሚገኙበትን ይህንን መድረክ በማዘጋጀቱ ኩራት ይሰማዋል›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡*

*ለሁለት ቀናት በቆየዉ በዚህ ዐዉደ ርዕይ ለገንዘብ ድጋፍ ተደራሽነት፤ በግሉ ዘርፍ በጤናዉ መስክ ለተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች፤ አቅራቢዎችና ንዋይ ድጋፍ ለሚሰጡ አካላት ቅንጅት መድረክ የተመቻቸበት ከመሆኑም በላይ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የግሉ ዘርፍ የሀገሪቱ ቤተሰብ ዕቅድና ሥነተዋልዶ ጤና ፤ በህፃናትና እናቶች ጤና እንዲሁም በኤች አይ ቪ/ኤድስና ሳንባ ነቀርሳ መካከልና ህክምና ዙሪያ በተቀመጡ ሀገራዊ ግቦች ላይ ያተኮረ በግሉ ዘርፍ በፖሊሲ አዉጪዎችና በለጋሾ መካከል ቀጣይነት ያለዉ ትብብር እንዲኖር አስችሏል፡፡*

*###*

በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በጤናዉ መስክ የተገኙ ዉጤቶች ማጠናከር (ሾፕስ) የተሰኘዉ ፕሮጀክት የግሉ ዘርፍ በጤናዉ መስክ በሚኖረዉ ድርሻ ላይ ያተኮረ አለም አቀፍ *የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ጥረት ሲሆን፤ በዋናነት በግሉ ዘርፍ በኩል በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትና ሥነተዋልዶ ጤና ፤ በህፃናትና እናቶች ጤና እንዲሁም በኤች አይ ቪ/ኤድስና በሌሎች የጤና መስኮች የተሻለ የምርትና አገልግሎት አቅራቦት፤ጥራትና ተደራሽነት በሚኖርበት ሁኔታ ከመንግስታዊ ያልሆኑና ለትርፍ ከተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት የሚሰራ ነዉ። በኢትዮጵያ ፕሮጀክቱ ባንኮች በሃገሪቱ ጠንካራና መጠነ ሰፊ የሆነ የጤና አገልግሎት እንዲኖር ለግሉ ዘርፍ ባንኮች ብድር የሚሰጡበትና አዳዲስ የጤናዉ ዘርፍ እንቅስቃሴዎችን እንዲደጉሙ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል።*

###